DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

## የደረጃ ሁለት መመሪያ

## ኮሮና ቫይረስ 2019 (COVID-19): በቀጠሮ ለሚደረግ ቀዶ ጥገና መመሪያ

በደረጃ ሁለት ወቅት ፣ ህዝብ እና ቢዝነሶች ለሁሉም የተጋላጭነትን እድል ለመቀነስ አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የደህንነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ ። ይህ መመሪያ በደረጃ ሁለት ውስጥ በቀጠሮ የሚደረጉ ህክምናዎችን እና የድንገተኛ ጊዜ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ምክር ይሰጣል ።

እነዚህን አገልግሎቶች በሚሰጡበት ጊዜ፣ **የ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይመከራሉ፤ በእነዚህም መካከል የ COVID-19 የስርጭት አደጋን ለመቀነስ እንዲረዳ እነሱም: የህክምና ሠራተኞች፣ ሕሙማን እና ጎብኚዎች፡፡** ለበለጠ መረጃ ይመልከቱ፣ https://coronavirus.dc.gov/phasetwo.

### ለታካሚ የሚሰጥ አትኩሮት

- **የአምቡላሪቶሪ የቀዶ ጥገና ማዕከላት እና ሆስፒታሎች (በቂ የሆነ በአዳር የሚደረግ የታካሚ አገልግሎት የመስጠት አቅም መኖሩን ላረጋገጡ) ከክሊኒካዊ እና ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች አንፃር ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ሊከናወኑ የሚችሉትን ሁሉንም ህክምናዎችን ማከናወን ይችላሉ፡፡**
- እንደነዚህ ያሉትን የቀዶ ጥገናዎችን እና ህክምናዎችን እንደገና መጀመር ከዘገየ የጤና እንክብካቤ ጋር ተያይዞ የከፋ የታካሚ ውጤቶችን ለመቀነስ ፣ የታካሚዎችን የቀዶ ጥገና አደጋ እድል ለመቀነስ ፣ ህብረተሰቡንና የኢያትሮጄኒክ ስርጭትን ለመቀነስ እንዲሁም PPE ን በጥሩ ሁኔታ ማዋል በሚሉት ሁኔታዎች ሊተነበዩ ይገባል፡፡
- ለሚታዩት የከፋ የታካሚ ውጤቶችን ለሚቀንሱ ህክምናዎች የዘገየ የጤና እንክብካቤ እና ከአነስተኛ የመተላለፍ አደጋ ጋር ተያይዞ፤ ቅድሚያ መስጠትዎን ይቀጥሉ።
- በአዳር የሚደረጉ እና በቀጠሮ የሚደረጉ የታካሚ አገልግሎቶችን አስፈላጊነት ለመቀነስ የሚገኝ ከሆነ የቴሌሜዲስን እና ሌሎች አማራጭ የሕክምና አገልግሎቶችን መጠቀምዎን ይቀጥሉ።
- ከ COVID-19 ጋር ተዛማጅ የሆኑ ምልክቶች ያሉዋቸዉ እንደሆነ ሁሉንም ታካሚዎች በስልክ ያጣሩ ፡፡ ታካሚው የ COVID-19 ምልክቶች እንደታዩበት ያሳወቀ እንደሆነ፣ የሚቻል ከሆነ ታካሚው እስኪያገግም ድረስ ድንገተኛ ያልሆኑ ቀዶ ጥገናዎችን አለማድረግ።
- ታካሚዎች እና ጎብኚዎች ከጎበኙበት ቀን ጀምሮ በ 14 ቀናት ውስጥ በ COVID-19 የተያዙ እንደሆነ ለተቋሙ ማሳወቅ አለባቸው ፡፡

### የድርጅቶች አትኩሮት

- ሁሉንም ታካሚዎች እና ጎብኚዎች የ COVID-19 ምልክቶች እንዳሉባቸው በመግቢያ ላይ ይፈትሹ (ለምሳሌ ፣ የሙቀት መጠን ምርመራ ፣ የበሽታው ምልክቶች መጠይቅ)፡፡ **የ COVID-19 ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ትኩሳት (በግምት ወይም 100.4 ዲግሪ ፋራናይት) ፣ ብርድ-ብርድ ማለት ፣ ሳል ፣ የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር ፣ ድካም ፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም ፣ ራስ ምታት ፣ አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት ፣ የጉሮሮ መቁሰል ፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ ፣ ተቅማጥ ፣ ወይም ደግሞ ጥሩ ያልሆነ የጤና ስሜት።**
- ታካሚዎች እና ጎብኚዎች ወደ ተቋሙ ሲደርሱ የፊት መሸፈኛን እንደለበሱ በማረጋገጥ የግብአት ቁጥጥርን መተግበር። አንድ ጎብኚ ወይም ታካሚ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ ሳያደርግ ወደ ጤና ተቋማት ቢመጣ ፣ አቅርቦቶቹ ያሉ እንደሆነ ለግብአት ቁጥጥር የፊት ጭምብሎች ሊያገለግሉ ይችላሉ።
- እንደ ምልክቶች እና በተገቢው ቋንቋ የተዘጋጁ ፖስተሮች ያሉ የሚታዩ ማስጠንቀቂያዎችን መግቢያዎች እና በዋና ዋና ስፍራዎች ላይ ለእጅ ንጽህና ፣ ለትንፋሽ ንፅህና (የጨርቅ የፊት መሸፈኛ አጠቃቀምን ጨምሮ) ፣ እና ለሳል ጊዜ መሸፈንን ለማሳየት መለጠፍ፡፡

- ለታካሚው ደህንነት እና እንክብካቤ አስፈላጊ ለሆኑት ጎብኚዎች ብቻ የተቋሙን መግቢያ መገደብ ፡፡
- ጎብኝዎች በታካሚው ክፍል ወይም ሌሎች በተጠቀሱ የተቋሙ ስፍራዎች ብቻ መገኘት አለባቸው።
- ተቋማት በቂ የሆነ የሳሙና እና የውሃ እና 60-95% የአልኮል ይዘት ያለው በአልኮል ላይ የተመሠረተ የእጅ ማጽጃ አቅርቦቶችን ማቅረብ አለባቸው።
- ተቋማት በመጠባበቂያው ስፍራዎች ውስጥ የመቆያ ጊዜን መቀነስ፣ ወንበሮችን ቢያንስ በ 6 ጫማ ርቀት ላይ ማስቀመጥ እና የታካሚ መጠንን አነስተኛ ማድረግ አለባቸው።
- እንደ የጀርም አልባ ማቀነባበሪያ፣ ላቦራቶሪ እና የምርመራ ምስል ያሉ የቀዶ ጥገና ሂደት አገልግሎቶችን የሚደግፉ ሌሎች የተቋሙ ቦታዎች በተቋሙ መመሪያ መሰረት ለማከናወን ዝግጁ መሆን አለባቸው።

## የአሰሪዎች አትኩሮት

- ሰራተኞች ሲታመሙ ወደ ሥራ መምጣት የለባቸውም።
- ለትኩሳት እና ከ COVID-19 ጋር ለተያያዙ ምልክቶች ሠራተኞች በየጊዜው እራሳቸውን እንዲከታተሉ መጠየቅ አለባቸው።
- አንድ የሰራተኛ አባል በስራ ላይ እያሉ የታመሙ እንደሆነ ወዲያውኑ እንክብካቤ መስጠታቸውን ማቆም፣ ለአሠሪያቸው ማሳወቅ ፣ ተቋሙን ለቀው መውጣት እና ከጤና አጠባበቅ አቅራቢያቸው ጋር መማከር አለባቸው ፡፡
- ተቋሙ ተለዋዋጭ ፣ ቅጣትን የማያሳይ እና የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ የሚያስችላቸውን የህክምና ፈቃድ ፖሊሲዎችን መተግበር አለበት ፡፡ የትምህርት ቤት ወይም የሕፃናት መንከባከቢያ ስፍራዎች መዘጋት ያሉባቸው እነደሆነ ፣ ወይም የታመሙ የቤተሰብ አባሎቻቸውን የሚንከባከቡ ከሆነ ከልጆቻቸው ጋር አብረው መቆየት ለሚፈልጉ ሰራተኞች ደግሞ የፈቃድ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን አለባቸው ፡፡
- ስለ COVID-19 ተቀጣሪዎቹን ማስተማር ለበለጠ መረጃ https://coronavirus.dc.gov/ ን ይመልከቱ።

## የኢንፌክሽን ቁጥጥር እና የግል የመከላከያ መሣሪያዎች

- ተቋማት ህክምና ማድረግ የሚችሉት በሚያከናውኑት የህክምና ብዛት እና አይነት ላይ መሰረት ባደረገ መልኩ በቂ የግል የመከላከያ መሣሪያዎች (PPE) ካሉዋቸው እና በማህበረሰቡ ውስጥ የ COVID-19 እንቅስቃሴ የሚጨምር ከሆነ ተገቢውን አቅርቦት ለማረጋገጥ በቂ ከሆኑ ብቻ ነው ፡፡
- የጤና አገልግሎት ሰጭዎችና ሰራተኞች በሁሉም ጊዜ የቀዶ ጥገና የፊት ጭምብሎች መልበስ አለባቸው።
- ሰራተኞቻቸው ከፍተኛ በአየር ላይ የመተላለፍ አደጋ ያላቸውን ሂደቶችን ሲያከናውኑ እንደ N95 መተንፈሻዎች እና የፊት መከላከያዎች ያሉ ተገቢ የመተንፈሻ መከላከያ መጠቀም አለባቸው።
    - የመተንፈሻ መሳሪያዎች የህክምና ግምገማዎችን ፣ ስልጠናዎችን እና ተገቢ ምርመራን የሚያካትቱ በመተንፈሻ አካላት ጥበቃ ፕሮግራም ውስጥ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።
- ሠራተኞች ከህክምና በፊት፣ በህክምና ወቅት እና በኋላ በተቋም ፖሊሲ መሰረት PPE መልበስ አለባቸው።
- ሰራተኞች በታካሚዎች መካከል PPE መቀየር እና በማውለቅ ሂደቱ ወቅት ወደ ባዶ እጅ ተላልፈው ሊሆኑ የሚችሉ ማንኛውንም በሽታ አምጪ ተዋህስያን ለማስወገድ PPE ከመልበስ በፊት እና ከማውለቅ በኋላ የእጅ ንጽህና መጠበቅ አለባቸው።
- ሰራተኞች በተለይም ከሁሉም ታካሚ እና ኢንፌክሽን ሊያስተላልፉ ከሚችሉ ቁስ አካላት ጋር ንክኪ ከማድረግ በፊት እና በኋላ እንዲሁም ጓንትን ጨምሮ PPE ከመልበስ በፊት እና ከማውለቅ በኋላ ጥብቅ የሆነ የእጅ ንጽህናን መጠበቅ አለባቸው።
- PPE የማድረጊያ እና የማወለቂያ ቦታዎች እና ለ PPE ቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች መመስረት አለባቸው።

## ማጽዳት እና ከጀርሞች ነፃ ማድረግ

- ከእያንዳንዱ ታካሚ በኋላ እና በተቋም ፖሊሲ መሰረት የአካባቢያዊ ማጽዳት እና ከጀርም ማስወገጃ ሂደቶች በቋሚነት እና በትክክል መከተላቸውን ያረጋግጡ።

- ለተጠረጠረ ወይም የተረጋገጠ COVID-19 ላላቸው ታካሚዎች ህክምናዎችን የሚያከናውኑ ከሆነ ተላላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ቅንጣቶችን ለማስወገድ በቂ የአየር ለውጥ እነዲኖር የሚያስችል ተገቢ የከፍል የቆይታ ጊዜን ያረጋግጡ።

- በ SARS-CoV-2 ላይ ለመጠቀም በEPA እየወጣ ባለ የቫይረስ በሽታ አምጪ ተህዋስያን መርሃግብር ስር ብቁ የሆኑ በ EPA ለተመዘገቡ ፀረ-ጀርሞችን በ EPA ድህረገጽ ላይ ዝርዝር N ይመልከቱ።

## ህንጻን ከግምት ውስጥ ማስገባት

- የቆሸሸ ውሃን ለማፅዳት እና በንጹህ ውሃ ለመተካት የውሃ ስርዓቶች እንዲታጠቡ ያድርጉ፡፡ ይህ ወደ ውሃው ውስጥ ገብተው ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም ብረቶች (ለምሳሌ ሊድ) ያስወግዳል እናም የሌጂይፐኔር በሽታ እና ከውሃ ጋር የተዛመዱ የሌሎች በሽታዎችን አደጋ ይቀንሳል። ደረጃ ለዚህ ሂደት CDC ድህረ ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡
    - https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/php/building-water-system.html.

ከዚህ በላይ ያሉት የመመሪያዎች ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እየተሻሻሉ የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ እባክዎን https://coronavirus.dc.gov/ ን ለወቅታዊ መረጃ በመደበኛነት ይጎብኙ፡፡